የሰ/መ/ቁ. 119557

ሐምሌ 19 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች ፡- አቶ ማናለው ተካ - ተወካይ ታዴ ተካ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እቴነሽ ተካ - ተወካይ አቶ ተስፋው ከቤ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳዩ የተጀመረው በምስራቅ ጎጃም ዞን እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ወላጅ አባቴ አቶ ተካ አንተነህ በስጦታ ያስተላለፉልኝን መሬት አመልካች በጉልበት በመያዝ እየተጠቀመበት ስለሚገኝ እንዲለቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የሰጠው መልስ ክስ የቀረበበት መሬት ላይ ለተጠሪ የስጦታ አስተላላፊ ከሆኑት ከአቶ ተካ አንተነህ ጋር አስቀድሞ የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የእርቅ ስምምነት ያለቀ በመሆኑ የተጠሪ ስጦታ አድራጊ በስጦታ ለማስተላለፍ የማይችሉ ከመሆኑም በላይ መሬቱ ለአመልካች እናት ጭምር የተሰጠ ስለሆነ የተጠሪ ክስ የአመልካችን መብት የሚነካ ስለሆነ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አቶ ተካ አንተነህ አስቀድሞ ያደረጉት የእርቅ ስምምነት መሬቱን በስጦታ ከማስተላለፍ የሚከለክል ባለመሆኑ አመልካች መሬቱን ለተጠሪ ሊለቅ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም አቶ ተካ አንተነህ መሬቱን በተመለከተ አስቀድመው በእርቅ የጨረሱ

ስለሆነ መሬቱን ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

ተጠሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲሁም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው የክልሉ ሰበር ችሎት አባ ተካ አንተነህና አመልካች ያደረጉትን ስምምነት ይዘት የአባ ተካ አንተነህ የይዞታ መሬት አመልካች ይዞ እያረሰ ሰብል እንዲሰጥ የተስማሙበት እንጂ የአባ ተካን መሬት ወደ አመልካች የማስተላለፍ ህጋዊ ውጤት ያለው ስምምነት አይደለም፤ የክፍሉ መሬት አስተዳዳርም አስቀድሞ የአባ ተካ መሬት ለአመልካች ያለማስተላለፉን በመገንዘብ ለተጠሪ የተሰጠውን ስጦታ መዝግቦታል በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 30 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በክልሉ ሰበር ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ:- በአባ ተካ አንተነህ እና በአመልካች መካከል የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው እርቅና በፍርድ ቤት የፀደቀው ስምምነት ባለበት ሁኔታ እንዲሁም በዚሁ ስምምነት መሰረት እንዲፈፀም የአፈፃፀም ትእዛዝ ባለበት ሁኔታ ያደረጉት ስምምነት መሬቱን ወደ አመልካች የማስተላለፍ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይህ ውሳኔ ተሽሮ የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው ስምምነት እንዲፈፀም ለተጠሪ የተደረገው ስጦታ እንዲሻር በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት የካቲት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች ጥያቄ ለክርክር መነሻ የሆነው መሬት በእርቅ ስምምነት ያገኙት ለተጠሪ ልለቅ አይገባም የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ በስጦታ ያገኙትና በአግባቡ በማስረጃ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ለክርክሩ መነሻ የሆነው የመሬት ይዞታ አመልካች ከስጦታ አድራጊ አባ ተካ የእርቅ ስምምነት የነበራቸው መሆኑ እና ተጠሪም በስጦታ የተሰጣቸው መሆኑ አከራካሪ ነጥብ አይደለም፡፡ የሚያከራክረው

በአመልካችና በአባ ተካ መካከል የተደረገው የእርቅ ስምምነት ይዘት ላይ ነው፡፡ ስለሆነም የእርቁ ስምምነት አመጣጥ መመርመሩ ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡

አመልካች ለአባ ተካ የመሬት ይዞታ እያረሰ በአላባ እንዲጠቀም በነበራቸው ስምምነት አለመግባባት በመፈጠሩ ጉዳያቸው ወደ ፍርድ ቤት ደርሶ ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ባደረጉት የእርቅ ስምምነት ሊቋጭ እንደቻለ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ አባ ተካ የአማራ/ብ/ክ/መ/ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ አንቀጽ 15/1/፣17 ማንኛውም ሰው የይዞታ መብቱን በስጦታ ለማስተላለፍ በሚፈቅደው መሰረት በሚመለከተው አካል ቀርበው ለአሁን ተጠሪ በስጦታ መስጠታቸውን በክፍሉ ተመዝግቦ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑ የፍሬ ነገር የማጣራትና የማስረጃ የመመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋጋጠ ነው፡፡

የእርቁ ስምምነት ይዘት አባ ተካ የመሬት ባለይዞታ በመሆን አመልካች ደግሞ በጉልበቱ እያረሰ የአላባ የመጠቀም መብት የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ የእርቅ ስምምነት ለአባ ተካ የመሬት ይዞታቸው በስጦታ ለፈለጉት ሰው የማስተላለፍ መብታቸውን የሚገድብ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ስምምነቱ አመልካች የአባ ተካ ይዞታ እስካለ ድረስ የአላባ የመጠቀም መብት የሰጠ ነው፡፡ ይዞታው ለሌላ ሰው ከተላለፈ ተጠሪ በአላባ የመጠቀም መብቱም የማቋረጥ ውጤት ነው ያለው፡፡ አመልካች ሌላ መከራከሪያ ነጥብ አባ ተካ ለተጠሪ ያደረጉት ስጦታ የእናቴ ይዞታ ጭምር ነው በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የመሬት ይዞታው ለአባ ተካ ተለክቶ የተሰጣቸው መሆኑን ባደረጉት ማጣራት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ችሎትም በፍሬ ነገር የማጣራትና የመመዘን ስልጣን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ስልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል በተያዘው ጉዳይ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.03-40156 ጥቅምት 9 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0116362 ታህሳስ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.37155 ሚያዝያ 2 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ በመሻር የእነብሴ ሳርምድር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.01-012499 ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ከዚህ ፍርድ ቤት የእነብሴ ሳርምድር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0112499 የተጀመረው አፈፃፀም ተላልፎ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስተዋል፡፡ የሚመለከው አካል ይፃፍ፡፡

3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገብ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ